# "እየሱስ ክርስቶስ ጎንደሬ ሆነ እንዴ"?
# እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ!

## *ይድረስ ለአባ ቀውስጦስ፤*

*የአባ ቀውስጦስ ምን ዓይነት እግር ነው? እሪ በይ አገሬ ጉድሽ ተዋህዶ!*
*ይህንን ስንል፤*

*(1) ቀደም ሲል በዲሲ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያናችን የተፈጠረውንና ያስከተለውን መዘዝ እናስታውሳለን። በዚህ ወቅት እርስዎ ባስነሱት ነገር በቤተክርስቲያን አባቶቻችንና በምዕመናን መካከል በተፈጠረው አሳፋሪ ውጥረት በቤተክርስቱያን ቅዱስ ስፍራ ለሁሉም ሰላም በምትሆነው የጥበቃ ኃይል የተጠራበት ዘግናኝ ጊዜ እየዘገነን እያለ፣*

*(2) ዛሬ ደግሞ በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ቄሶች በቄሶች ላይ ተነሳስተው (ድንጋይ በድንጋይ ላይ ማለታቸው ይሆን፣ አታስቁን!) የተወሰኑ ቄሶች ወደ ቤተእግዚአብሔር አምልኮ የግል ፀሎት እንኳ እንዳይገቡ በጥበቃ ኃይል የሚታገዱበት የውርደት ጊዜ ላይ ደረስን። እንዴት የሰው ልጅ በአምላኩ ፊት እንዳይንበረከክ ነፃነቱን ይገፈፋል? አይ ጊዜ! የ21ኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ ሴራና ኪሳራ። ለመሆኑ ማ ማንነው ቤተክርስቲያንን የሚከለክለው?*

*(3) ሌላው የእርስዎ ማዘዣ ጣቢያ በሆነችው በቨርጂኒያ ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ቄስና በሰበካ ጉባኤው መካከል በተፈጠረው ችግር ከቄሱ ላይ የድምጽ ማጉሊያ መነጋገሪያውን በመንጠቅ የተደረገ ግብግብና ከአምስት ሰዓታት የፈጀ የሞት የሽረት 'ሪንግ' ቀረሽ የ'ሬስሊንግ' ትርዒት የእርስዎ ውጤቶች ናቸው።*

*ይህ አስከፊ በውግዘት መለያየት የፈጠረው የመነካካስና የመበላላት የእግዚአብሔር መንፈስ ከቤተክርስቲያን የተነሳበት ክፉ ጊዜ ቢኖር አባ ቀውስጦስ ቦታውን ከረገጡበት ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ የተከሰተ የሰሞኑ አብይ ጉዳይ ነው። ታዲያ ቤተክርስቲያናት እንዲህ እየታመሱና ምዕመናን እያለቀሱ ሰሞኑን ለእግረ ደረቁ ለአባ ቀውስጦስ (አባቶቻችን የበትርም እንኳ ገድ አለው ይላሉ) በዲሲ ደብረ ምህረት ቤተክርስቲያን ንሴብሆ ብሎ ጉድዎን ለመሸፈን ከበሮ መጉሰሙ፣ ማስጎሰሙ በእግዚአብሔር ላይ ማሾፍ? ምዕመናኑን መናቅ? ወይስ ሌላ? ከበሮም ለካ ያለ ቦታው ለውሸት ሲመታ ያስጠላል። በስፍራው ይህንን ተገኝተን አየንና ገረመን። ይህ ንቀት መቼ ነው የሚያቆመው? አባ ቀውስጦስ እስከመቼ የፍቅርና የዕርቅ መንፈስ ከላይዎት ተገፎ ይኖራሉ? ምናለበት በሀገረ ስብከትዎ ቢቀመጡ? ለምን እየመጡ ሰላምን ይነሳሉ? ይህ ያስጠይቅዎታል!*

እስኪ ምዕመናኑ ወይም ተመልካች ዘወር ብሎ እርስዎ ውግዘትዎን ሳያሰሙና እዚህ አገር ሳይመጡ የነበረውን ጊዜ ወደ ኋላ ሲያስታውስ ሰላም ነበርን፤ ሌት ተቀን ደክመን ሰርተን እግዜብሔርን አምልከን አመስግነን እቤታችን እንገባ የነበርን፤ ታዲያ ልጅዎችዎ ተውን ስንልዎት ለምን አይገባዎትም! የግድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በአውደ ምሕረቱ ይህንን እንድንልዎት ነው የሚሹት? አንተ ታውቃለህ ብለን በልባችን አምቀን የያዝነውን ብሶት ብንተነፍስ የሚቋቋሙበት የመንፈስ ጥንካሬና ኃይል ይኖራታልን? ወይስ ያች መከረኛ እምባዎት ትመጣ ይሆን? ወይንስ ሰላም የሌለው ሰላምን አይሰጥም ሆኖብዎት ይሆን? ሁሉም በገደብ ሲሆን ጥሩ ነው። አሁን ትዕግስታችን ዳር ደርሷል። ለበቃኝ በቃኝ ነው። በእምነታችንና በዚህ ሀገር ህጋዊ ኑሮአችን ያገባናል። ሁከትን አንሻም።

ያለፈው ቤተክርስቲያናችንን በታሪክ የከፈለ የለያየን ውግዘት ተጨባጭነት የሌለው ለመወጋገዝ የማያበቃ የጎጠኝነት ፊታውራሪ በሆነ ውግዘትዎ አይጸጸቱምን? በንስሐ ከውንድሞችዎ ጋር ዕርቅን ከመፈለግ ይልቅ ምን ነካዎት አባታችን? እርስዎ ተሳስተው ሌሎችን ብፁአን አባቶቻችንንም አሳስተው እነዚያ ዛሬ ያሳሳቷቸው ብፁአን አባቶች እያዘኑ እየተጸጸቱ ያሉበት ነገር መሆኑን አላወቁምን? ይህንንስ ነግረዎት የለም እንዴ? እግዚኦ መሐረነ!

በቅርቡ ከሶስት ሳምንታት በፊት በአንድ ኢንተርኔት ድረ-ገፅ “ይድረስ ለአባ ቀውስጦስ” በሚል ምዕመናን ያቀረቡልዎትን ጥያቄ አይተናል። እኛም ጉዳዩ ስቦናል። እኛም ይድረስ ለአባ ቀውስጦስ ብለናል። መልስ እንሻለን።

ለእየሩሳሌም ገዳማት ማደሻና ንብረቶች መግዣ የተዋጣውን ገንዘብ “በሉት” የሚል አላነበብንም። ይህንንም ያደርጋሉ ብለንም እኛም አልገመትንም። ምናልባት ገንዘቡ የዋለበትን ባለማሳወቅዎት ይሆናል ለትችት የዳረገዎት። ምዕመናኑ የበለጠ ለመስራት ለእምነቱ ካለው ቀናኢነት ተነሳስቶ ሲጠይቅ መልስ ይሻል። ዳሩ ግን እርስዎ ማን ስለሆኑ ነው መልስ የማይሰጡበት? የሚመጡትም እኮ ገዳም ሳይሆን እኛጋ ነው። እረሃብ እንደ ምፅዓት ቀን ሆኖ ህዝባችንን ከበሽታና እርስዎ ካስቀመጡት እንቅፋት (ውግዘት) በመለያየት ፍቅር ማጣት ያለመተዛዘን ጋር ተዳምሮ ሞት እያረገፈው በኢትዮጵያ ቀኑ ጨልሞ ዋይታ ብቻ ሲሆን ከቦታ ቦታ የሚበሩትም እኮ በእኛ ገንዘብ መሆኑ አይሰማዎትምን? ያ ገንዘብ የስንቱን ነፍስ ሊታድግ እንደሚችል አያውቁ ይሆን?

የእርስዎ ላስ ቬጋስ፣ ሂውስተን፣ዲሲ… ወዘተ መንሸራሸር ፋይዳ ያለው ይመስልዎታልን? በፍፁም እንደውም እኝህ ፍቅር የለሽ ቤተክርስቲያናችንን በውግዘት የከፈሉ እያለ ሰው ሲጠቋቆምቦት ቢያውቁ ምን ይሰማዎት? ምናልባት እግዚያብሔር የሚሰጠው ትልቁ ነገር ጊዜ ነውና በጊዜው ተጠቅመው በረሃብ በሞት አፋፍ ያለው እንኳ የቤተክርስቲያኗን አንድነት አይቶ አመስግኖ ተስፋውን በእግዚያብሔር እንዳደረግ የዘላለም እንቅልፋን እንዲያሸልብ ሰላምን ቢሿት? እርቅን ቢፈልጓት? ፍቅርን እንዲከተሏትና ተምሳሌት እንዲሆኗት የትኛው ጠበል እንውሰድዎ?

ይህንን ከማድረግ ይልቅ “በእግዚአብሔር ቃል ተጠቅመው የሚጽፉብኝና የሚያዋርዱኝ የጎንደሬዎች ቤተክርስቲያን ናቸው” ሲሉ አያፍሩም? ይህንን ሲናገሩ

ሰለሰማንዎት አፈርንብዎት፤ “እየሱስ ክርስቶ ጎንደሬ ሆነ እንዴ”? እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ!!! ጌታችንና መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ሁለቱን እጁን የዘረጋውና በመስቀል ላይ ሕይወቱን በቤዛነት አሳልፎ የሰጠው ለመላው የሰው ልጅ ዘር መሆኑና ቤተክርስቲያንን በደሙ የዋጃት መሆኑ ተካደ እንዴ? ጉድ እኮ ነው። ቤተክርስቲያን ቅድስት አንዲት በክርስቶስ የሆነች የጸናች የእየሱስ ክርስቶስ ነች፤ እራሷም እየሱስ ክርስቶስ ነው። የትም ዓለም ትመስረት መቼም ቢሆን።

አባታችን አባ ቀውስጦስ የመንፈስ አባት ተብለው ሥልጣን ፈላጊ፣ጎጠኛ ዘረኛ፣ቂመኛ ስሜትዎትን “እንደምታ ዘአባቀውስጦስ ወአባ ገሪማ” ብለነዋል። ክፉ ስሜትዎት መንፈስዎትን እስከ መቼ ተጭኖት ይኖራል? ወይንስ እየቀሰቀሱ ሌላውን የመለያየት ኪሳራ ውስጥ በመጨመር ለንስሐ ሳይበቃ እንደታሰረ እንዲወድቅና እርስዎ ፓትሪያርክ ለመሆን ይፈልጋሉን? በሞቱ ይንገሩን። ምኞት አይከለከልም፤ ፈቃድ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ከ7 ዓመታት በፊት እየሩሳሌም በመኖሪያዎ ተገኝተን ግድግዳው ላይ የሰቀሉትን የፎቶዎ አነሳስ፣ አለባበስና የጌጥ ድርድር ብዛት አይተን የገረመን ጊዜም ነበር። ያኔም ፍላጎትዎንና ስሜትዎን ተረድተናል። ተገናኝተናል። አሁንስ አወቁን ይሆን? ወይንስ እነኛ የፈረደባቸው እነ እከሌ ይሉ ይሆን?

(4) እውነትን እውነት ያነሳዋል እንዲውሉ ሜሪ ላንድ የሚገኘው የደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ገና ይህንን አገር እርስዎ ሳያውቁት በዚህ አገር የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን መሆኑ እየታወቀ አሁን በእርስዎ ልክፍት የሚናወጡት አዲስ ቤተክርስቲያናት ሳይከፈቱ የደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ለረዥም ዓመታት ታቦቱ በመንበሩ ላይ በክብር ከተቀመጠና እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ሆኖልን እያለን ቤተክርስቲያኑን እግዚአብሔር ኃያል ሆኗቸው ከጎጠኝነት የፀዱ እጅግ ጠንካራ የቦርድ አባላትና ምዕመናን ያሉት መሆኑን ካለማስተዋል መርጋት ካቃታቸው ብዙ ነገር ከሚነገርባቸው ጳጳስም ለመሆን ላይ ታች ከሚረግጡት አባ ገብረወልደ በሚባሉት ወኪልዎ አማካይነት ጎተት ብለው ለመግባት ለብዙ ጊዜ ሞክረው ያልተሳካልዎት ሲሆን፤

ነገር ግን ቤተክርስቲያኑን ለመያዝ በዚህ ዘዴ ይሆናል ብለው ባሰቡት ማለትም ለደብረገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን “ያዘዛችሁትን ታቦት አምጥቼላችኋለሁ” ብለው ቤተክርስቲያኑ በማያውቀው ሁኔታ እርስዎ አባ ቀውስጦስ ባመጡት መዘዝ ጠንካራው ቦርድ፣ እውነተኛ ካህናትና ምዕመናን ባደረጉት ወሳኝ የማይረሳ ተጋድሎ ሁኔታውን አጣርቶ ግልጽ  በማድረግ ሊከሽፍብዎት ችሏል። የቤተ ክርስቲያኑም ሆነ የመዕመናኑ ልብ በነገሩት ግለሰብ የሚንቀሳቀስ መስሎዎት ውስጥ ውስጡን ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲጋበዙ ያሳሰቡት ሁሉ ከንቱ ሆኖ እርስዎ ባመጡት መዘዝ ከጉዳዩ ጋር ከቤተክርስቲያኑ ዕውቅና ውጭ በማይሆን አካሄድ ከእርስዎ ጋር የተባበሩትን ሁለት አገልጋዮች ሊቀ ዲያቆናት ጌታሁንና የእኛን ምስኪን የአባ ገብረ ሕይወትን የአንድ ወር ደመወዝ መቀጣት ምክንያት ሆነዋል። ሊቀ ዲያቆናት ጊታሁን በድቁና አገልግሎቱ ወቅት ያለው ድምፅ ተወዳጅነትና ምስጉንነት ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም።

ነገርን ነገር ያነሳዋልና እንዲሉ የየደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ቦርድ አባላትና ምዕመናን በተለይም ከወደ ኒውዮርክ ቤተክርስቲያናን

ለማናጋት በአንድ ብስለት በሌለው ጮርቃ ጭንቅላት አማካይነት የተሰማራው ዘማሪ ተብዬ ግለሰብ የየደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ከላይ እስከ ታች "መናፍቃን" ናችሁ በማለት ቦርዱንና ምዕመናኑ በጥላቻ ልክፍት ለመከፋፈል ያደረገውን መሰሪ ተግባር በማክሸፍም ቦርዱና መዕመናን የወሰዱት እርምጃ እሰየው አበጃችሁ የሚያሰኝ ነው።

ከእውነታው ውጭ ያለቦታው "መናፍቅ" የሚለውን በግልባጭ የወቅቱ ማጣፊያ ያጠረባቸው የቤተክርስቲያን አንድነትን የማይፈልጉ ከፋፋዮች በጥቅም አደሮች ዲያቢሎሳዊያን የሚጠቀሙበት ቃል መሆኑን ልንረዳ ችለናልና የተዋሕዶ ልጆች ልብ ልንለው ይገባል።

አባታችን አባ ቀውስጦስ የእርስዎን የውግዘት ድራማ ተከተሎ ከማንም በላይ ተመግባችሁ በልታችሁ ሳይሆን ያላችሁን የሥልጣን ጥማት ለመግለጽ ቃል ቢያጥረው "ሆዳሞች" (ድርሳነ ዘመምህር ዘበነ) ያለውን በሰማን ጊዜ እንዴት እንዲህ ይላል ብለን አዝነን ነበር። አሁን ግን ሥልጣን ወንበር ፈላጊነት ለካ ሆድ አለው! ሆዱም መወጋገዝ፣መለያየት፣ጨካኝነት፣ዘረኝነት፣ ቂመኝነትና ፍቅር ማጣት የቤተክርስቲያን እንቅፋት መሆኑን እነሆ አሁን የእርስዎን ሥራ ስናይና ሲገባን ተረዳን። ይህንንም "ሆዳሞች" ብለሃልና ይቅርታ በለን አልያም ሥልጣነ ክህነት አታገኝም በሃገርም ውስም መስበክ አትችልም ተብሎ ልጅዎችዋ ቅዱስ ወንጌል ለመስበክ የታገዱበት የወቅቱ ያልታደለች አገር በእናንተ አየን፣ ይገርማል!

በእርግጥ ከመቸኮሉና ካልሆኑ መካሪዎቹ ጭምር መምህር ዘበነ ብዙ ጊዜ ተሳስቷል። አይተናል እንደማንኛውም ሰው ይሳሳታል። መምህሩ ይታበያል። እራሱን ብቻ ሰባኪና አዋቂ አድርጓል። አገራችን ስንት ምርጥ አንቱ የተባሉ ሰባኪ ወንጌላዊያን የተሰጣቸውን ፀጋ ለይተው የተገነዘቡ እንዳሏት ባለማስተዋል እራሱን ብቻ በሊቅነት ከምሮ የወንጌል ቁንጮ አድርጓል። ያለእርሱ ማንም አያውቅም። ፀጥ ባለው የቅዳሴ ሰዓት እንኳ በአገልግሎት ጨፍልቀው ሊሰሩት የሚችሉትን ክህናትን ጣልቃ እየገባ "ይህ ይሁን፣ ያ ይሁን" ሲልና በቤተ መቅደስ በፍርሃት እግሩን ሳይጠብቅ ሲፈራገጥበት የዘውትር አስተውሎታችን ነው።

ገንዘብ መለመኑንማ ተክኖበታል። ገንዘብ ከአገልግሎት በላይ እየሰለጠነበት መጥቷል። ይህ መምህር ቀደም ሲልም በዲሲ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ሲያደርጉለት ከነበረው ጠቀም ያለ ገንዘብ በተጨማሪ የሙዳይ ምፅዋዕት ገንዘን ላይ ድርሻዬ በመቶ ሲለካ 30% አነሰኝ በማለት የስብከት አገልግሎቱን ማቋረጡና ሌሎች ብዙ ነገሮች ማንሳት ይቻላል።

ቢሆንም በእምነታችን እስከአሁን ድረስ በመምህርነት የሰጠውን የስብከት አገልግሎትና ውለታ ግምት ውስጥ በማስገባት (እኛ እንኳን ይመነኩሳል ብለን ነበር) ዓለምን ቀመሳት በተፈጥሮ ህግ አዙሪት በውስጧ ይኖራልና። ዳሩ ግን ክህነት ለመቀበል መስፈርቱን አሟልቶ እንኳን ጠይቆም ወደ ስልጣነ ክህነት ማዕረግ የሚወስደውን መንገድ አባቶች ታዘጋጁለት ነበር። ነገር ግን አውጋዦች ይቅርታ አታውቁምና ከእግዚአብሔር መንገድ ውጭ በግለሰባዊ ፍላጎት የክህነት ማረጋገጫ ለመስጠት

ከለከላችሁት። ይህንን ትርዒት ወደ ፊት የመንመጣበት ይሆናል። አሁንም በትርዒቱ ውስጥ አዲስ አበባ ይገኛልና።

(5) ከዚሁም ጋር አባታችን አባ ቀውስጦስ የደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያንን በእርስዎ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ብለው የሰሩት ሌላው ታላቁ የታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግዎት ስህተት የኢትዮጵያን ቤተክርስቱያን ቅርስ የሆነውን ኢትዮጵያን በእውነት የሚያውቋትን ከማወቅም አልፈው የተሰውላትን የሰማዕቱን አባታችን የአቡነ ጴጥሮስን መስቀል ለግለሰብ በመስጠት ከሃገር አስወጥተዋልና ከሥልጣንዎትም በላይ ነውና ጊዜ ሳይሰጡ እንዲመለስ ያደርጉ ዘንድ ታሪክ ከመጠየቁ በፊት እንጠይቅዎታለን።

ያን አሳልፈው በመስጠትዎ ጭምር ሊሆን ይችላል "ሆዳሞች" የተባሉት። በዚህ የሚያዘው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንና ሕዝብ እንጅ ማንም አይሆንም። ሊሆንም አይችልም። ሕዝብና ቤተክርስቲያንም የሃገርን ቅርስ ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ያሸጋግራሉ እንጅ ለከንቱ ውዳሴ የግለሰብ ጉራ መቸርቸሪያ አሳልፈው አይሰጡም። ከቀደሙ አባቶቻችንና ከቤተክርስቲያን ትውፊትም ቢሆን ይህንን አልተማርንም። ይህ አገር ቀርሶ ከመስጠት አይተናነስም። ይህ ቅርስ የበደል፣ የግፍ፣ የደም ውጤት፣ የእምነትና አርበኝነት፣ የሰማዕትነት ቅዱስ ምልክት ማስታወሻ መስቀል "ኢትዮጵያዊ ሆኖ" ይጥፋ ተብሎ ይሆን እንዴ የተሰጠው? እግዚኦ መሃረነ! ይህ እንዲመለስ ለቤተክርስቲያንችም ለሕዝባችንም ጥሪ እናስተላልፋለን።

ስለዚህም ዛሬም የምንጠይቅዎት ከእንድምታ ዘአባ ቀውስጦስ ወአባ ገሪማ ወጥተው በአዲስ ጉልበት የእየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ሐዋሪያ ተምሳሌ ይሁኑን። አይምሽብዎት! ፍቅርና ዕርቅን ይፈልጉና ይቅር ባይነትን ያስተምሩን። ለቤተክርስቲያ የሚበጀው እርሱ ነውና። ይህንን የጣሉትን ይቅርታ፣ ዕርቅና ፍቅር ካላነሱትና ከወንድሞችዎ ጋር በሕብረትና በአንድነት ካልቆሙ የተዋህዶ አባት ነኝ አይበሉ። ተዋህዶ የንስሐ፣ የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት ቤት ነችና።

የተፈጸመው በውግዘት የመለያየት "የጉስቁልና ምልክት" ስህተት ትርዒት እስከመቼ ይቀጥላል? እስከመቼ ቤተክርስቱያን ለጥቃት ዒላማ ሆና ተመቻችታ ተዳክማ ትቆይ ይሉናል? ይህ የመለያየት ግጭትና ዘረኝነት የአባ ቀውስጦስ የእርስዎ ቀኖና ወይንስ ዶግማ? በመለያየት ጎጠኛ ፈረስ ተጭኖ የምፅዓት ቀንን የማቅረብ ፍልስፍና ወይንስ ሌላ? ስለሆነም ያለፈው ላይመለስ ሁሉንም ችግር ላይ ጥሎ አልፏልና እባክዎትን አባ ቀውስጦስ መፅሃፉን ባይተገብሩትም እንኳ እንደሚያውቁት "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" መዝ 67፡31 ነው እንጂ እንደ "እንድምታ ዘአባ ቀውስጦስ ወአባ ገሪማ ኢትዮጵያ ወደ መለያየት እጅዎችዋን ትዘረጋለች" አይልምና ስለእግዚአብሔር ብለው በመሳሌነት ወደ አንድነት ወደ ተዋህዶ ይምጡ። ስማችንንም ስራችንም ግብረ ታሪካችንም ተዋህዶ ነውና ስምዎትን በእውነተኛ ሥራ ያድሱ። የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ለመታደግ ዛሬ ጥሪ አቅርበንልዎታል።

ሌላው ምስጋናችን ምንም ገንዘብ የማዋጣት ባለድርሻ ብንሆንም በአገራችን በምዕመናን ጥረት በእርስዎ አስተባባሪነት በመገንባት ላይ ያለው የአባታችን የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ መታሰቢያ ቤተክርስቲያን ከመጀመሪያው ከሃሳቡ ጀምሮ ያስደስተንና

እሰየው ያልንበት ስለሆነ ምስጋናችን ይድረስዎት። ይበርቱ። መስቀሉን በቦታው መመለስዎትን ግን አይርሱ!

ማጠቃለያ፤ ምንም ይሁን ምን የፈለገውን ያህል መሰሪዎች ያስቀመጡት እንቅፋት የዝቅጠትና የጉስቁልና ምልክት የሆነው መለያየት ውጣውረዱን ቢያበዛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ግን እንደ እግዚአብሔር ቸርነት ወደቀደመ ሥፍራዋ ያለጥርጥር ትመለሳላች። የአንድነት ብርሃንም ይወጣል።

ስለሆነም እኛ ዛሬ ከኢትዮጵያ የበቀልን ኢትዮጵያዊ ኦርቶዶክሳዊ የተዋህዶ የቁርጥ ቀን ልጅነታችንን ዛሬ እየገለጽንልዎት ወደፊትም እግዚአብሔር ቢፈቅድ በእምነታችን ሥራ ባለው ነገር ሁሉ ዕርቅና ሰላም ወርዶ ቤተክርስቲያን አንድ ሆና ወደቀደመ ቦታዋ እስክትመለስ የቤተክርስቲያናችን ነገር ዕለት ዕለት ስለሚያስጨንቀን እስከሞት ድረስ እናታችን ተዋህዶ አለንልሽ፣ ጭንቅሽ ይሰማናል፣ ስቃይሽ ስቃያችን ሆኖ ከአንች በፊት እንሙት እያልን ያለ መለያየት በነገር ሁሉ የተዋህዶ ወታደሮች በተጨባጭ መኖራችንን ለአባ ቀውስጦስና ለመሰሎችዎ እናረጋግጣለን። "እየሱስ ክርስቶስ ጎንደሬ ሆነ እንዴ"? እግዚኦ መሃረነ ክርስቶስ?

"እየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው ነው"፣ እብ 13፡ 8።

ስለሁሉም ነገር እግዚያብሔር ይመስገን!!!

ከፍኖተ ጽድቅ ዘበኢትዮጵያ
ሰሜን አሜሪካ
ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም.